የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No 52
ADDIS ABABA 16h July, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፭/፪ሺ፩ ዓ.ም

ለነቀምቴ-በደሌ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተደረገውን የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፯፻፷፩

CONTENTS

Proclamation No. 645/2009

Arab Bank for Economic Development in Africa Agreement for Financing the Nekemete-Bedele Road Project Ratification Proclamation……… Page 4761

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፭/፪ሺ፩

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለነቀምቴ-በደሌ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፲ሚሊዮን አሜሪካን ዶላር /አስር ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፪ ቀን ፪ሺ፱ በዳካር የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፭ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለነቀምቴ-በደሌ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት ጋር የተደረገውን የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፭/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 645/2009

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in an amount of ten million United States Dollars (USD 10,000,000) for financing the Nekemete-Bedele Road project was signed in Dakar on the 12th day of May 2009;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 2nd day of July,2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Agreement for Financing the Nekemete-Bedele Road Project Ratification Proclamation No. 645/2009".

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፪ ቀን ፪ሺ፱ በዳካር የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብ ድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አሥር ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement signed on May 12th 2009 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of ten million United States Dollar (USD 10,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of July, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**